የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አሥራሦስተኛ ዓመት ቁጥር ፷፩
አዲስ አበባ ነሐሴ ፳፱ ቀን ፲፱፻፺፱

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

13th Year No. 61
ADDIS ABABA 4th September, 2007

ማ ው ጫ

አዋጅ ቁጥር ፭፻፶/፲፱፻፺፱ ዓ.ም

የኢትዮጵያ የምርት ገበያ ማቋቋሚያ አዋጅ.... ገጽ ፫ሺ፰፻፺፰

CONTENTS

Proclamation No. 550/2007

Ethiopia Commodity Exchange Proclamation No. .Page 3898

## አዋጅ ቁጥር ፭፻፶/፲፱፻፺፱

## የኢትዮጵያ ምርት ገበያን ለማቋቋም የወጣ አዋጅ

የሀገሪቱን ግብርና በገበያ ላይ ወደተመሠረተ የአመራረት ሥርዓት ማሸጋገር ድህነትን ለመቀነስ ወሳኝ መሣሪያ መሆኑ በመንግሥት ዋና ዋና ፖሊሲዎች የተገለጸ በመሆኑ፤

አነስተኛ የግብርና አምራቾች ወቅታዊ የገበያ መረጃ እንዲያገኙና ለምርታቸው የተሻለ ዋጋ መደራደር እንዲችሉ በማድረግ በገበያው ላይ ያላቸውን ተሳትፎ ማሳደግ ተገቢ በመሆኑ፤

ለዚህም ቀልጣፋ፣ ሥርዓት ያለውና ወጥነት ያለው የግብርና ምርቶችን የገበያ ሥርዓት ማቋቋም አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥቱ አንቀጽ ፶፭ /፩/ መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ

### ፩. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "የኢትዮጵያ የምርት ገበያ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር ፭፻፶/፲፱፻፺፱" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

## PROCLAMATION NO. 550/2007.

## A PROCLAMATION TO PROVIDE FOR THE ESTABLISHMENT OF THE ETHIOPIA COMMODITY EXCHANGE

**WHEREAS** transforming the country's agriculture to market oriented production system has been envisaged by the major policies of the government as critical tool for poverty alleviation;

**WHEREAS** it is important to promote increased participation of small agricultural producers by providing up-to-date market information and enabling them to negotiate better prices for their products;

**WHEREAS** to these ends it is found necessary to establish an efficient, orderly and unified marketing system for agricultural commodities;

**NOW, THEREFORE,** in accordance with Article 55 Sub-Article (1) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

## PART ONE
## GENERAL

### 1. Short Title

This Proclamation may be cited as the "Ethiopia Commodity Exchange Proclamation No. 550/2007."

ያንዱ ዋጋ
Unit Price

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. ፹ሺ፩
Negarit G. P.O.Box 80001

## ፪. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በቀር፣ በዚህ አዋጅ ውስጥ፤

፩/ "የክፍያ መፈጸሚያ ተቋም" ማለት የምርት ገበያው ወይም በባለሥልጣኑ እውቅና ያገኘ የአገር ውስጥ ባንክ ወይም ተመሳሳይ የፋይናንስ ተቋም ነው፤

፪/ "የክፍያና ርክክብ አፈጻጸም" ማለት አንድ ድርጅት በአገናኝነት ወይም በአቀራራቢነት የሚሠራበት ሥነ ሥርዓት ሆኖ፣ ድርጅቱ ለግብይቱ አፈጻጸም የገዢና የሻጭን ሚና በመውሰድ በተዋዋይ ወገኖች የሚሰጡትን ትዕዛዞች የሚያስታርቅበትና የገንዘብ ክፍያና ርክክብ የሚፈጸምበት አሠራር ነው፤

፫/ "ባለስልጣን" ማለት በአዋጅ ቁጥር ፭፻፶፩/፲፱፻፺፱ የተቋቋመው የምርት ገበያ ባለሥልጣን ነው፤

፬/ "ምርት" ማለት ከሌላ አንድ ዓይነት ምርት ጋር መለዋወጥ የሚችል ምርት ነው፤

፭/ "የምርት ገበያ" ማለት ወጥ ሆነው በተዘጋጁ ምርት ነክ ውሎች ግብይት የሚፈጸምበት የምርት ገበያ ነው፤

፮/ "ውል" ማለት ለምርት ገበያ ግብይት ሲባል አንድን ምርት ለመግዛት ወይም ለመሸጥ ወጥ ሆኖ የተዘጋጀና የምርቱን መጠን፣ ዋጋ፣ ደረጃ፣ ተፈጻሚ የሚሆንበትና የምርቱ ርክክብ የሚፈጸምበትን ቀን በዝርዝር የሚያካትት ስምምነት ነው፤

፯/ "ዳታ" ማለት የኤሌክትሮኒክስ ዳታ ልውውጥን፣ የኤሌክትሮኒክስ መልዕክትን፣ ቴሌግራምን፣ ቴሌክስንና ቴሌኮፒን ጨምሮ በኤሌክትሮኒክስ፣ በኦፕቲካል ወይም በተመሳሳይ ዘዴዎች የሚመነጭ፣ የሚላክ፣ የሚደርስ ወይም የሚከማች መረጃ ነው፤

## 2. Definitions

Unless the context otherwise requires, in this Proclamation:

1/ "clearing institution" means the Ethiopia Commodity Exchange or domestic bank or similar financial institution recognized by the Ethiopia commodity Exchange Authority;

2/ "clearing and settlement" means the procedure by which an organization acts as an intermediary and assumes the role of a buyer and seller for Exchange trade transactions in order to reconcile orders between transacting parties, and insures the physical or financial settlement of the transaction;

3/ "authority" means the Ethiopia Commodity Exchange Authority established under Proclamation No. 551/2007.

4/ "commodity" means a product which is interchangeable with another product of the same kind;

5/ "commodity exchange" means an exchange where standardized commodity-linked contracts are traded;

6/ "contract" means a standardized agreement to buy or sell a specified commodity, detailing the amount, grade and price of the commodity and the date on which the contact will mature and become deliverable for purposes of trading on the Exchange;

7/ "data message" means information generated, sent, received or stored by electronic, optical or similar means including, but not limited to, electronic data interchange, electronic mail, telegram, telex and telecopy;

፰/ "የኤሌክትሮኒክ ፊርማ" ማለት ከመረጃ መልዕክቶች ጋር በተያያዘ ፈራሚን ለመለየትና በመልዕክቱ የተካተተው መረጃ በፈራሚው የፀደቀ ወይም ተቀባይነት ያገኘ መሆኑን ለማመልከት ጥቅም ላይ የሚውል በመረጃ መልዕክት ላይ የተለጠፈ ወይም ከመልዕክቱ ጋር የተያያዘ በፌሌክትሮኒክስ ፎርም ያለ መረጃ ነው፤

፱/ "የግብይት ፈጻሚ" ማለት ለሌሎች ወይም ለራሱ ሲል የምርት ግብይት ውሎችን በመግዛትና በመሸጥ ንግድ ሥራ የተሰማራ በባለ ሥልጣኑ ዕውቅና ያገኘ ማንኛውም ሰው ነው፤

፲/ "ለወደፊት የሚፈጸም ውል" ማለት በተቆረጠ የወደፊት ቀን የምርቱ ርክክብ የሚፈጸምበት ምርትን ለመሸጥ ወይም ለመግዛት የሚደረግ የምርት ግብይት ውል ነው፤

፲፩/ "የመያዢያ ገንዘብ" ማለት ግዢ ፈጻሚዎች በገበያ ላይ ለሚፈፅሙት አንድ ግብይት በመያዣነት ሊያስቀምጡት የሚገባ ገንዘብ ነው፤

፲፪/ "አባል" ማለት በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፰/፩/ የተመለከተውን የምርት ገበያ የአባልነት መመዘኛ የሚያሟላ ማንኛውም ሰው ነው፤

፲፫/ "ሚኒስቴር" ማለት የግብርናና የገጠር ልማት ሚኒስቴር ነው፤

፲፬/ "ሰው" ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤

፲፭/ "ወዲያውኑ የሚፈጸም ውል" ማለት ርክክብና ክፍያ ወዲያውኑ የሚፈጸምበት የምርት ግብይት ውል ነው።

## ክፍል ሁለት
## የኢትዮጵያ የምርት ገበያ

### ፫. መቋቋም

፩/ የኢትዮጵያ የምርት ገበያ /ከዚህ በኋላ "የምርት ገበያ" እየተባለ የሚጠራ/ ሙሉ ባለቤትነቱ የመንግሥት የሆነና የሕግ ሰውነት ያለው የገበያ ተቋም ሆኖ ተቋቁሟል።

፪/ የምርት ገበያው በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፰ የተመለከቱትን የሚያሟሉ ቋሚ መቀመጫዎች ያሏቸው አባላት ይኖሩታል፤

8/ "electronic signature' means data in electronic form, affixed to or logically associated with, a data message, which may be used to identify the signatory in relation to the data message and to indicate the signatory's approval of the information contained in the data message;

9/ "exchange actor" means any person recognized by the Authority who engages in the business of buying and selling exchange trade contracts for others or for his own account;

10/ "futures contract" means an exchange traded contract to buy or sell a commodity for delivery of the physical good at a specified future date;

11/ "margin" means the funds which must be deposited by exchange actors as collateral for a given transaction for the exchange;

12/ "member" means any person that fulfills the requirements of Article 8(1) of this proclamation;

13/ Ministry" means the Ministry of Agriculture and Rural Development of the Federal Democratic Republic of Ethiopia;

14/ "person" means any physical or juridical person;

15/ "spot contract" means an exchange trade contract for immediate delivery of and payment for the commodity

## PART TWO
## THE ETHIOPIA COMMODITY EXCHANGE

### 3. Establishment

1/ The Ethiopia Commodity Exchange (hereinafter 'the Exchange') is hereby established as a wholly state owned market institution having its own legal personality.

2/ The Exchange shall have Members, with permanent seats, who meet the necessary requirements set out in article 8 of this Proclamation.

፫/ የምርት ገበያው ባለቤትነት፣ አባልነትና የሥራ አመራሩ የተለያዩ ይሆናል፤

፬/ የምርት ገበያው በዚህ አዋጅ፣ በምርት ገበያ ባለሥልጣኑ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር ፭፻፶፩/፲፱፻፺፱ እና በሌሎች አግባብ ባላቸው ሕጎች የሚተዳደር ይሆናል።

**፬. ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን**

ሚኒስቴሩ የምርት ገበያው ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን ይሆናል።

**፭. ዋና መሥሪያ ቤት**

የምርት ገበያው ዋና መሥሪያ ቤት በአዲስ አበባ ሆኖ እንደአስፈላጊነቱ ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤቶችን በሌሎች ቦታዎች ማቋቋም ይችላል።

**፮. ዓላማዎች**

የምርት ገበያው የተቋቋመበት ዓላማዎች የሚከተሉት ናቸው፣

፩/ የገዢዎችን፣ የሻጮችንና የአገናኞችን ፍላጎት በማርካትና የኢትዮጵያ አነስተኛ አምራቾች የገበያ ተሳትፎን በማሳደግ ውጤታማ፣ ግልጽ አሠራርን የተከተለና በሥርዓት የሚመራ የግብይት ሥርዓት መፍጠር፤

፪/ የግዢ ጥያቄ አቅርቦትና የግዢ ጨረታ ውድድር ተቀናጅተው በግልፅ ጨረታ መድረክ በቃል በማስተጋባት ተጫራቾች ጨረታ በግላጭ በሚያካሂዱበት የመገበያያ መድረክ ወይም የኤሌክትሮኒክስ ትዕዛዝን በሚያቀነባብር ሥርዓት ወይም ሁለቱም የሚካሄድበት የንግድ አሠራር ሥርዓቶችን መዘርጋት፤

፫/ የምርት ግብይትን የሚመለከቱ መረጃዎችን ለመያዝ፣ ለመከታተል፣ ለሕዝብ ለማሠራጨት የሚያግዝ በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የተደገፈ የቢሮ አሠራርን ተግባራዊ ማድረግ፤

፬/ ደረጃ ለወጣላቸው ምርቶች ግብይት መሠረት የሚሆኑ ወጥነት ያላቸው ውሎችን ማዘጋጀት፤

፭/ የምርት ደረጃ የምስክር ወረቀትንና ዋስትና ያለው የዕቃ ማከማቻ ደረሰኝን መሠረት በማድረግ ግብይት ማካሄድ፤

3/ The exchange shall be demutualized with a separation of ownership, membership, and management.

4/ The exchange shall be governed by this proclamation, the proclamation to establish the Commodity Exchange Authority No. 551/2007, and other relevant laws.

**4. Supervising Authority**

The Ministry of Agriculture and Rural Development shall be the supervising authority of the Exchange.

**5. Head Office**

The exchange shall have head office in Addis Ababa and may have branch offices elsewhere, as may be necessary.

**6. Purpose**

The purposes for which the Exchange is established are:

1/ to create an efficient, transparent, and orderly marketing system that serves the needs of buyers, sellers, and intermediaries, and that promotes increased market participation of Ethiopian small scale producers;

2/ to provide a centralized trading mechanism in which offers to sell and bids to buy are coordinated through a physical trading floor with open outcry bidding or an electronic order matching system or both;

3/ to provide automated back office operations to record, monitor, and publicly disseminate information on Exchange transactions;

4/ to provide standardized grade-specific contracts as the basis of Exchange trading;

5/ to conduct trading on the basis of product grade certificates and guaranteed warehouse receipts;

፮/ ግዴታን ባለመወጣት የሚያጋጥሙ አደጋዎችን ለመቀነስ በምርት ገበያው የሚከናወኑ ግብይቶችን ክፍያና ርክክብ የመፈጸም፤

፯/ ክርክሮች በሽምግልና ዳኝነት አማካይነት የሚታዩበትን ሥርዓት መዘርጋት፤

፰/ ወቅታዊ የገበያ መረጃዎችን ለሕዝቡ ማቅረብ፤

፱/ የምርት ገበያውንና የአባላቱን ህልውናና ጤናማ አሠራር የተጠበቀ መሆኑን ለማረጋገጥ ገበያውን በቅርብ መከታተል፣

፲/ የአደጋ ቁጥጥር አስተዳደርን ተግባራዊ በማድረግ በአጠቃላይ የገበያ ሥርዓቱ ላይ አደጋ እንዳይከሰት መከላከል።

## ፯. ካፒታል

የምርት ገበያው የተፈቀደ ካፒታል ብር ፪፻፶ ሚሊዮን /ሁለት መቶ ሃምሳ ሚሊዮን/ ሲሆን ብር ፺ ሚሊዮን /ዘጠና ሚሊዮን/ በገንዘብና በዓይነት ተከፍሏል።

## ፰. ስለ አባልነት

፩/ አባል ለመሆን የሚፈልግ ማንኛውም ሰው፣

ሀ/ በባለሥልጣኑ መመሪያ መሠረት በግብይት ፈጻሚነት ዕውቅና ያገኘ፣ እና

ለ/ ለራሱ ወይም ለሌላ ሰው ሲል በምርት ግብይት ሥራ የተሰማራ፣

መሆን ይኖርበታል።

፪/ የምርት ገበያው በሚደነግገው ሁኔታዎች መሠረት የምርት ገበያው በነጻ ሊተላለፍ የሚችሉ ቋሚ መቀመጫዎች ያሏቸው አባላት ይኖሩታል።

፫/ በምርት ገበያው የተዘጋጁና በባለሥልጣኑ የፀደቁ የምርት ገበያው የውስጥ ደንቦች ለአባልነት ብቁ የሚያደርጉ መመዘኛዎችን ይደነግጋሉ።

፬/ በምርት ገበያው የውስጥ ደንቦች የተመለከቱትን የአባልነት መመዘኛዎች የሚያሟላ ማንኛውም ሰው የአባል መቀመጫ ሊገዛ ይችላል።

6/ to clear and settle all transactions conducted on the Exchange to minimize default risk;

7/ to provide a mechanism for dispute resolution through arbitration;

8/ to provide timely market information to the public'

9/ to carry out market surveillance to ensure the integrity of the members and of the market;

10/ to avoid Contingent risk to the market through implementing risk management by employing proper management mechanism;

## 7. Capital

The authorized capital of the exchange is Birr 250,000,000 (Two Hundred Fifty Million) of which Birr 90,000,000 ( Ninety Million) is paid in cash and in kind.

## 8. Membership

1/ A member shall be any person:

a) recognized as an exchange actor, under the directives of the Authority; and

b) engaged in the trading of exchange commodities either for his own account or for the account of others.

2/ The Exchange shall have members with permanent seats which are freely transferable, subject to the terms and conditions that may be prescribed by the Exchange.

3/ The Exchange rules and by-laws to be developed by the Exchange and approved by the authority shall set requirements necessary for membership.

4/ Any person that fulfills membership requirements set by the Exchange rules and by-laws may purchase a membership seat.

፭/ አባል መሆን በምርት ገበያው የውስጥ ደንብ በተመለከቱት መብቶችና ጥቅሞች የመጠቀም መብት ይሰጣል።

፮/ አባልነት ከሌሎች መብቶች በተጨማሪ በምርት ገበያው የመገበያየት መብት ይሰጣል።

**፱. <u>የምርት ገበያው፣ የአባላቱና የሦስተኛ ወገኖች ተጠያቂነት</u>**

፩/ የምርት ገበያው ሹማምንቶቹ፣ ዳይሬክተሮቹና ሠራተኞቹ ለሚፈጽሙት ድርጊት ወይም ግድፈት ተጠያቂ ነው።

፪/ የምርት ገበያው ከዚህ በታች ከተመለከቱት ጋር በተያያዘ ለሚያጋጥሙ ጉድለቶች ተጠያቂ ነው፣

ሀ/ ከምርት ገበያው የግብይት ሥርዓት፣

ለ/ ከምርት ገበያው የመረጃ ሥርጭት ሥርዓት፣

ሐ/ በምርት ገበያው ከሚካሄዱ የማከማቻ መጋዘኖች፣ የማከማቻ መጋዘኖች ደረሰኞችና የማከማቻ መጋዘኖች ደረሰኞች ማስቀመጫ፣

መ/ በምርት ገበያው ከሚሰጡ የደረጃና የምርት ማረጋገጫ ሰርቲፊኬት፣

ሠ/ በምርት ገበያው ከሚከናወኑ የክፍያና ርክክብ አፈጻጸም፣

፫/ የምርት ገበያው ከንብረቱ በላይ በዕዳ አይጠየቅም።

፬/ አባላት የምርት ግብይት ውሎችን ሳይፈጽሙ ሲቀሩ አግባብ ባለው ሕግ መሠረት ተጠያቂ ይሆናሉ።

፭/ አባላት በስማቸው ተወክሎ የሚሠራ ሰው ለሚፈጽመው ድርጊት፣ ግድፈት ወይም ጉድለት ተጠያቂ ይሆናሉ።

፮/ በምርት ገበያው የተመሰከረላቸው ወይም ከምርት ገበያው ጋር የሥራ ግንኙነት ኖሯቸው ማከማቻ መጋዘንን፣ የማከማቻ መጋዘኖች ደረሰኞችንና የማከማቻ መጋዘኖች ደረሰኞች የማስቀመጥ ሥራን የሚያካሂዱ የደረጃና የምስክርነት ማረጋገጫ የሚሰጡ፣ ክፍያን የሚያስፈጽሙ ወይም ሌሎች ሥራዎችን የሚያከናውኑ ሦስተኛ ወገኖች አግባብ ባላቸው ውሎችና ሕጎች መሠረት ተጠያቂ ይሆናሉ።

5/ Membership shall entitle a member of the Exchange to exercise such rights and privileges as provided under the Exchange rules and by-laws.

6/ Membership shall, among other things, confer a right to trade on the Exchange

**9. Liability of the Exchange, Members, and Third parties**

1/ The Exchange shall be liable for any acts or omissions of its officers, directors, and employees.

2/ The Exchange shall be liable for any failures relating to:

a) Exchange trading system;

b) Exchange information dissemination system;

c) Exchange-operated warehousing, warehouse receipting, and warehouse receipt central depository;

d) Exchange-operated grading and product certification;

e) Exchange-operated clearing and settlement

3/ The Exchange shall not be liable beyond its total asset.

4/ The members shall be liable for the non performance of exchange- trade contracts in accordance with relevant law.

5/ The members shall be liable for acts, omissions or failures of any agent acting on their behalf.

6/ Third parties certified or affiliated with the Exchange to perform warehousing, warehouse receipting, warehouse receipt central depository, grading and certification, clearing and settlement or other functions shall be liable in accordance with the relevant contracts and laws.

**፲. የምርት ገበያው አቋም**

የምርት ገበያው፣

፩/ የዳሬክተሮች ቦርድ፣

፪/ አንድ ዋና ሥራ አስፈጻሚ፣ እና

፫/ አስፈላጊው ኃላፊዎችና ሠራተኞች፣
ይኖሩታል።

**፲፩. የዳይሬክተሮች ቦርድ ጥንቅር**

፩/ የዳይሬክተሮች ቦርድ አሥራ አንድ አባላት የሚኖሩት ሲሆን ሰብሳቢውን ጨምሮ ስድስቱ በሚኒስቴሩ እንዲሁም አምስቱ በአባላት ይሾማሉ።

፪/ ዋናው ሥራ አስፈጻሚ ድምፅ የማይሰጥ የቦርድ አባል ይሆናል።

፫/ የቦርድ ዳይሬክተር የሹመት ወይም የምርጫ ዘመን ሦስት ዓመት ይሆናል። ሆኖም የቦርድ ዳይሬክተሩ እንደገና መሾም ወይም መመረጥ ይችላል።

፬/ የቦርድ ዳይሬክተሮች ሥራቸውን ሳያቋረጡ እንዲያከናውኑ ለማድረግ ለሁሉም የዳይሬክተሮቹ የሥራ ዘመን በአንድ ጊዜ እንዲያበቃ አይደረግም።

፭/ የቦርድ ዳይሬክተር ቦታ ክፍት በሚሆንበት ጊዜ ሥራውን የለቀቀው ዳይሬክተር በተሾመበት ወይም በተመረጠበት ሁኔታ ሌላ ሰው እንዲመረጥ የዳይሬክተሮች ቦርድ ጉዳዩን ሚኒስቴሩ ወይም የምርት ገበያው አባላት እንዲያውቁት ማድረግ ይኖርበታል።

**፲፪. የዳይሬክተሮች ቦርድ ሥልጣንና ተግባር**

የዳይሬክተሮች ቦርድ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፣

፩/ የምርት ገበያውን ዋና ሥራ አስፈጻሚ ይሾማል፣

፪/ የምርት ገበያውን በበላይነት ይቆጣጠራል፣

፫/ ለዋናው ሥራ አስፈጻሚ ተጠሪ የሆኑ ኃላፊዎችን ቅጥር፣ ምደባና ስንብት እንዲሁም ደሞዝና አበላቸውን ያፀድቃል፣

10. **Organization of the Exchange**

The Exchange shall have:

1/ a Board of Directors;

2/ a Chief Executive officer; and

3/ The necessary officers and staff.

11. **Composition of the board of Directors**

1/ The Board of Directors shall consist of eleven members, of whom six, including the chairperson, are appointed by the Ministry and five are elected by the members.

2/ The Chief Executive Officer shall be an additional ex-officio, non-voting, member of the Board of Directors.

3/ The term of appointment or election of a Board Director shall be for a period of three years. A Board Director shall be eligible for reappointment or re-election.

4/ In order to maintain the continuity of the activities of the Board of Directors, the terms of office of its Board Directors shall not expire at the same time.

5/ In the event of vacancy, the board of Directors shall bring the matter to the attention of the Ministry or members of the exchange so that another person is assigned in the same manner as the Board Director who has vacated his position

12. **Powers and Duties of the board of Directors**

The board of Directors shall have the powers and duties to;

1/ appoint the Chief Executive Officer of the Exchange;

2/ oversee the management of the Exchange;

3/ approve the employment, assignment and dismissal of the Officers of the Exchange accountable to the Chief Executive officer, including their salaries and allowance;

፬/ የምርት ገበያውን ኮርፖሬት ፕላንና ግብ፣ የምርት ግብይት አገልግሎት ክፍያ አደረጃጀት እና የአደጋ ቁጥጥር አስተዳደር ስትራቴጂን ያፀድቃል፣

፭/ የተጣራ ትርፍ ለተወሰኑ ስራዎች ወይም ለኢንቨስትመንት እንዲውል መደረጉን ያፀድቃል፣

፮/ የምርት ገበያው ካፒታል እንዲጨምር ወይም እንዲቀንስ ለሚኒስቴሩ ሃሳብ ያቀርባል፣

፯/ የምርት ገበያው የሂሣብ መዝገብ በአግባቡ መያዙን ያረጋግጣል፣

፰/ ለምርት ገበያው ኦዲተሮች የሂሣብ መግለጫ ያቀርባል፣

፱/ በየወቅቱ የፋይናንስና የሥራ እንቅስቃሴ ሪፖርቶች ለሚኒስቴሩ ያቀርባል፣

፲/ በባለሥልጣኑ መጽደቁ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ አባልነትን፣ ንግድን፣ የክፍያና ርክክብ አፈጻጸምን፣ የምርት ገበያውን የግብይት ውሎችን የሚመለከቱ የምርት ገበያውን ደንቦችና መመዘኛዎች ያወጣል፣ ያሻሽላል፣

፲፩/ በባለሥልጣኑ በፀደቀው የምርት ገበያው የውስጥ ደንብ በተደነገገው መሠረት የምርት ገበያውን አዲስ አባል ይቀበላል፣ ከአባልነት ያግዳል ወይም ያሰናብታል፣

፲፪/ በምርት ገበያው የተዘረጋው የሽምግልና ዳኝነት ሥርዓት በአግባቡ መስራቱን ያረጋግጣል፣

፲፫/ የቦርዱን ጸሐፊ ከምርት ገበያው ሠራተኞች መካከል መርጦ ይመድባል፣

፲፬/ የምርት ገበያውን በአግባቡ ለመምራት የሚረዱ የተለያዩ ኮሚቴዎችን ያቋቁማል፡

## ፲፫. የዳይሬክተሮች ቦርድ ኃላፊነት

፩/ የቦርዱ ዳይሬክተሮች ሥራቸውን በተገቢው ጥንቃቄ ማከናወን ይኖርባቸዋል።

፪/ የቦርድ ዳይሬክተሮች ሥራቸውን በአግባቡ ባለማከናወናቸው ምክንያት በምርት ገበያው ላይ ለሚያደርሱት ጉዳት በነጠላና በአንድነት ተጠያቂ ይሆናሉ።

4/ approve the corporate plan and targets, Exchange transaction fee structure, and risk management strategy of the exchange:

5/ approve the re-investment of net profits into specific activities or investments;

6/ propose to the Ministry to increase or decrease the capital of the exchange;

7/ ensure that proper books of accounts are kept for the exchange;

8/ submit books of accounts to the auditors of the exchange;

9/ submit periodic financial reports and reports on activities to the Ministry;

10/ prescribe and amend exchange rules and requirements regarding membership, clearing and settlement, and contracts traded on the Exchange, subject to approval by the Authority;

11/ admit, suspend, or expel a Member of the Exchange, according to the provisions of the Exchange rules and by-laws as approved by the Authority;

12/ ensure the proper functioning of dispute resolution mechanism provided by the exchange;

13/ select and assign its secretary from among the exchange staff;

14/ appoint various committees to facilitate the proper management of the exchange.

## 13. Liability of the Board of Directors

1/ Board Directors shall carry out their duties with due care.

2/ They shall be jointly and severally liable to the for damage caused to the exchange by their failure to properly carry out their duties.

፫/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፪/ ቢኖርም፣ ጉዳት ያደረሰው የዳይሬክተሮች ቦርድ ውሣኔ ሲተላለፍ በድምጽ የተለየ የቦርድ ዳይሬክተር በኃላፊነት ተጠያቂ አይሆንም።

## ፲፬. የዳይሬክተሮች ቦርድ የስብሰባ ሥነ ሥርዓት

፩/ የዳይሬክተሮች ቦርድ ቢያንስ በወር አንድ ጊዜ ይሰበሰባል።

፪/ አስቸኳይ ሁኔታ ሲያጋጥም ወይም ቢያንስ አራት የቦርድ ዳይሬክተሮች ወይም ዋና ሥራ አስፈጻሚው ሲጠይቁ ሊቀመንበሩ የዳይሬክተሮች ቦርድ ስብሰባ ይጠራል።

፫/ የዳይሬክተሮች ቦርድ የስብሰባ አጀንዳ ለቦርድ ዳይሬክተሮች በቅድሚያ መድረስ ይኖርበታል።

፬/ አብዛኞዎቹ የቦርድ አባላት ከተገኙ ምልዐተ ጉባዔ ይኖራል።

፭/ የዳይሬክተሮች ቦርድ ውሳኔ የሚያሳልፈው በድምፅ ብልጫ ይሆናል።

፮/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፭/ ድንጋጌ ቢኖርም የሚከተሉት ጉዳዮች የሚወሰኑት በሁለት ሦስተኛ የቦርድ ዳይሬክተሮች ድምጽ ይሆናል፣

ሀ/ ክፍያዎች፣
ለ/ የተጣራ ትርፍን እንደገና ኢንቨስት የማድረግ፣
ሐ/ የዋና ሥራ አስፈጻሚ ሹመት፣
መ/ የምርት ግብይት ደንቦችን ማፅደቅናማሻሻል፣

፯/ የዳይሬክተሮች ቦርድ እያንዳንዱን ስብሰባ በተመለከተ በስብሰባ ላይ በተገኙ የቦርድ አባላት የተፈረመ ቃለ ጉባዔ ይይዛል፣

፰/ የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆኖ የዳይሬክተሮች ቦርድ የራሱን የስብሰባ ሥነ ሥርዓት ደንብ ሊያወጣ ይችላል።

## ፲፭. የሚኒስቴሩ ሥልጣንና ተግባር

ሚኒስቴሩ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፣

፩/ በመንግሥት የሚወከሉ የቦርድ ዳይሬክተሮችን ይሾማል፣ ያነሳል፣

፪/ ለቦርድ ዳይሬክተሮች የሚከፈለውን አበል ይወስናል፣

3/ Notwithstanding Sub-Article (2) of this Article a Board Director shall not be liable if he has dissented from the decision of the Board of Directors which caused the damage.

## 14. Procedure of meeting of the Board of Directors

1/ The Board of Directors shall have a meeting at least once a month.

2/ The Chairperson shall call a meeting of the board of Directors, at any time, in cases of urgency or where at lest four board Directors or as the Chief Executive Officer may so request.

3/ The agenda of a meeting of the Board of Directors shall, in advance, be communicated to the Board Directors.

4/ There shall be a quorum where a majority of members are present.

5/ The Board of Directors shall take decisions by majority vote.

6/ Notwithstanding the provisions of sub-article(5) of this Article, decisions on:

a) fees;
b) re-investment of net profits;
c) appointment of chief Executive officer;
d) approval and amendment of Exchange Rules;

shall be made with two-thirds majority vote of the board Directors.

7/ The Board of Directors shall keep minutes for every meeting, which shall be signed by each Board Director present.

8/ Without prejudice to the provisions of this Article, The Board of Directors may adopt its own rules of procedure

## 15. Power and Duties of the Ministry

The Ministry shall have the powers and duties to:

1/ appoint and remove Government representative Board Directors;

2/ fix the allowances to be paid to Board Directors;

፫/ የውጭ ኦዲተሮችን አወዳድሮ አሸናፊውን ይመድባል፣

፬/ የምርት ገበያውን የተፈቀደ ካፒታል እንዲመደብ ያደርጋል፣

፭/ በኦዲተሮች የተመረመሩ የምርት ገበያውን የፋይናንስ ሪፖርቶች ያፀድቃል፣

፮/ ከምርት ገበያው የቀረበለትን የካፒታል ጥያቄንና የተጣራ ትርፍን እና እንደገና ኢንቬስት የማድረጊያ ፕላንን ያፀድቃል፣

፯/ የምርት ገበያውን አጠቃላይ ሥራ ይገመግማል፣ የግሉ ዘርፍ በባለቤትነት ስለሚሳተፍበት ሁኔታ ጥናቶች ለሚኒስትሮች ምክር ቤት ያቀርባል፣

፰/ የምርት ገበያውን ዓመታዊና የረዥም ጊዜ የምርት ገበያውን የኮርፖሬት ግቦችን ከቦርዱ ጋር በመመካከር ይወስናል፣ አፈጻጸማቸውን ይከታተላል፣

፱/ ለቦርዱ የተሰጠው ሥልጣንና ተግባር እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የመንግሥትን የባለቤትነት መብቶች ለማስከበር አስፈላጊ የሆኑ ሌሎች ሥራዎችን ያከናውናል።

## ፲፮. የዋና ሥራ አስፈጻሚው ሥልጣንና ተግባር

፩/ ዋናው ሥራ አስፈጻሚ የምርት ገበያውን ያደራጃል፣ ይመራል፣ ያስተዳድራል።

፪/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፩/ አጠቃላይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ ዋናው ሥራ አስፈጻሚ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፣

ሀ/ በዳይሬክተሮች ቦርድ መጽደቁ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ኃላፊዎችን ይቀጥራል፣ ይመድባል፣ ያሰናብታል፣

ለ/ በምርት ገበያው የውስጥ ደንቦችና አግባብ ባላቸው ሕጎች መሠረት የምርት ገበያውን ሌሎች ሠራተኞች ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል፣

ሐ/ የምርት ገበያው ከሦስተኛ ሰዎች ጋር በሚያደርጋቸው ግንኙነት ሁሉ የምርት ገበያውን ይወክላል፣

መ/ የምርት ገበያውን የሂሣብ መዛግብት በአግባቡ ይይዛል፣

3/ appoint external auditors;

4/ cause the allocation of the authorized capital of the exchange

5/ approve audited financial reports of the exchange;

6/ approve capital injection and net profit re-investment plan of the exchange,

7/ evaluate the overall performance of the exchange and submit studies regarding the participation of the private sector in its ownership to the council of Ministers;

8/ approve, in consultation with the Board, the annual and long-term corporate targets of the Exchange and follow up their implantation; and,

9/ without prejudice to the powers and duties given to the Board, perform other functions necessary for the protection of the ownership rights of the State.

## 16. Power and Duties of the Chief Executive Officer

1/ The chief Executive Officer shall organize, direct, and administer the Exchange.

2/ Without limiting the generality of sub-article (1) of this Article, the Chief Executive Officer shall have the powers and duties to:

a) employ, assign, and dismiss Officers, subject to approval of the Board of Directors;

b) employ and administer employees of the Exchange, in accordance with the internal rules of the Exchange and the appropriate laws;

c) represent the Exchange in all its dealings with third parties and in legal proceedings brought by or against it;

d) keep proper books of accounts of the Exchange, and open and operate bank accounts of the Exchange;

ሠ/ የምርት ገበያውን የሥራ ፕሮግራምና በጀት አዘጋጅቶ ለቦርድ ያቀርባል፣ ሲፀድቅም አፈጻጸሙን ይከታተላል፣

ረ/ እንደአስፈላጊነቱ የሥራ ማስኬጃ ገንዘቡን ለማሳደግ የአጭር ጊዜ የብድር ውሎች ይዋዋላል፣ የሚንቀሳቀስና የማይንቀሳቀስ ንብረትን በዋስትና ያስይዛል፣

ሰ/ እንደአስፈላጊነቱ በምርት ገበያው ህል ውና ላይ ተፅዕኖ የማያደርጉ ቋሚ ንብረቶችን ቦርዱን በማስፈቀድ ይሸጣል፣

ሸ/ ለምርት ገበያው ሥራዎች ቅልጥፍና አስፈላጊ ሆኖ በተገኘው መጠን ሥልጣንና ተግባሩን ለምርት ገበያው ኃላፊዎችና ሌሎች ሠራተኞች በውክለና ይሰጣል፣

ቀ/ በቦርዱ በሚወሰነው መሠረት ለዳይሬክ ተሮች ቦርድ ሪፖርት ያቀርባል፣

በ/ የዳይሬክተሮች ቦርድ ውሳኔን ይፈጽ ማል፣ እንዲፈጸም ያደርጋል፣

ተ/ በቦርዱ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል።

## ፲፯. የዋና ሥራ አስፈጻሚው ኃላፊነት

ዋና ሥራ አስፈጻሚው ሆነ ብሎ ወይም በቸልተኝነት በምርት ገበያው ላይ ለሚያደርሰው ጉዳት በሕግ መሠረት ኃላፊነት ይኖርበታል።

## ፲፰. የሥራ አመራር

፩/ የምርት ገበያው ገልለተኛ በሆነ በባለሙያ የሚመራ የሥራ አመራር ይኖረዋል።

፪/ በሚኒስቴሩ መፅደቁ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የምርት ገበያው የራሱ የሆነ የደሞዝ ስኬል ይኖረዋል።

## ክፍል ሦስት
## የምርት ገበያው አሠራር

## ፲፱. ስለአባላት የሥራ አመራር

፩/ የምርት ገበያው እያንዳንዱ አባል ተለይቶ የሚታወቅበትን መዝገብና አቋሙን የሚገልጽ ዳታ ቤዝ ይይዛል።

e) prepare and submit to the Board of Directors the work programme and budget of the exchange, and implement the same upon approval;

f) enter into short-term loan contracts for the purpose of raising working capital, borrow money on a long-term basis with the approval of the Board, and for those purposes, pledge or mortgage the movable or immovable property of the Exchange;

g) sell fixed assets that may not affect the existence of the Exchange with the approval of the Board of Directors;

h) delegate his powers to Officers and other employees of the exchange to the extent necessary for the efficient performance of the activities of the exchange;

i) submit report to the Board of Directors in the manner prescribed by the Board;

j) implement and cause the implementation of the decision of the Board of Directors; and

k) perform other activities assigned to him by the Board of Directors.

## 17. Liability of the Chief Executive Officer

The Chef Executive Officer shall be liable, in accordance with the law, for damages caused to the Exchange either intentionally or negligently.

## 18. Operational Management

1/ The Exchange shall have an autonomous and professional management.

2/ The Exchange shall have an independent salary structure, subject to approval by the Ministry

## PART THREE
## OPERATIONS OF THE EXCHANGE

## 19. Membership Management

1/ The exchange shall maintain a registration and identification of Members and a data base recording their status.

፪/ አባላት በምርት ገበያው የውስጥ ደንቦች የተደነገጉ የአባልነት መመሪያዎችን እንዲያከብሩ ያደርጋል።

፫/ የምርት ገበያው በአባላት ላይ የሚቀርቡ ቅሬታዎች የሚስናገዱበትን ሥርዓት ተግባ ራዊ ያደርጋል፤ ባለስልጣኑ በጠየቀ ጊዜ የሚቀርብ የቅሬታዎች መዝገብ ያደራጃል።

## ፳. ስለግብይትና የግብይት ሥርዓት

፩/ አባል ያልሆነ ወይም በአባል ተወካይነቱ ዕውቅና ያላገኘ ሰው በምርት ገበያው መገበያየት አይችልም።

፪/ ስለምርቱ ጥራት ወይም ደረጃ ከምርት ገበያው የምርት ምስክር ወረቀት ሳያገኝ እንዲሁም ስለምርቱ መጠን፣ ሁኔታና የማከማቻ መጋዘኑ የሚገኝበትን ቦታ የሚገልፅ የመጋዘን ማከማቻ ደረሰኝ ሳይኖረው ምርቱን በምርት ገበያው ለግብይት ማቅረብ የተከለከለ ነው።

፫/ የምርት ገበያው የግልፅ ጨረታ መድረክ በቃል በማስተጋባት ተጫራቾች በግላጭ ጨረታ የሚያካሂዱበት የመገበያያ መድረክ ወይም በርቀት የሚካሄድ በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የታገዘ የኤሌክትሮኒክ ንግድን መሠረት ያደረገ የንግድ ሥርዓት ያካሂዳል።

፬/ የምርት ገበያው ግብይትና የሚመለከቱ ውሎች የሚመዘገ ቡበትና ከአባላት ግብይት ጋር የተያያዙ ጉዳዮችን የሚያቀላጥፍ ድጋፍ ሰጪ ቢሮ ይኖረዋል።

## ፳፩. የገበያ መረጃዎችን ስለማሠራጨት

፩/ የምርት ገበያው ለሕዝብ በተለያዩ የመገናኛ ዘዴዎች ስለምርት ዋጋ ወቅታዊና የተሟላ መረጃ ይሰጣል።

፪/ የምርት ገበያው የዋጋ መረጃዎች እንዳይ ሰራጩ ወይም ዘግይተው እንዲሰራጩ ማድረግ አይችልም።

፫/ የምርት ገበያው የኤሌክትሮኒክ የዋጋ መረጃ ማሠራጫ ሥርዓት ያደራጃል።

2/ The exchange shall enforce membership rules as provided for under the Exchange rules and by-laws.

3/ The Exchange shall operate a system of filing complaints against Members and shall maintain a record of such complaints that shall be made available to the Authority.

## 20. Trading and Trading System

1/ It shall be unlawful for a person who is not a Member or a recognize agent of a Member to trade on the Exchange.

2/ It shall be unlawful for a commodity to be traded on the Exchange without the issuance of an Exchange product certificate as to the product quality and grade and of an Exchange warehouse receipt as to the product quantity, condition, and location of storage.

3/ The Exchange shall operate a single trading system which matches offers and bids based on open outcry on a physical trading floor or an automated system for remote electronic trading.

4/ The Exchange shall operate a back office in which transactions on contracts are recorded and which shall facilitate all matters related to members' trades

## 21. Market Information Dissemination

1/ The Exchange shall provide timely and complete price information to the public at large, through a variety of media.

2/ The Exchange may not withhold or delay price information for any reason.

3/ The Exchange shall operate a public electronic price information dissemination system.

## ፳፪. የምርት ግብይት ውሎች

፩/ የምርት ገበያው ከግብርና ምርቶች ጋር በተያያዘ ወዲያውኑ ወይም ወደፊት በሚፈጸሙ ውሎች ላይ ተመሥርቶ ይሠራል።

፪/ የምርት ገበያው የምርቱን ደረጃ፣ ምርቱ የሚቀርብበትን ቀንና ቦታ እንዲሁም ሌሎች የውል ድንጋጌዎች ያካተተ ውል ያዘጋጃል።

## ፳፫. ደረጃ ስለማውጣትና ስለምስክርነት ማረጋገጫ

፩/ የምርት ገበያው በገበያው ለሚካሄድ ግብይት ዓላማ የፀደቁ ወይም ተቀባይነት ያገኙ ደረጃዎችን ያወጣል፣ ይጠብቃል።

፪/ የምርት ገበያው ደረጃ የማውጣትና የማረጋገጥ ሥራ ያከናውናል ወይም ሌላ ሦስተኛ ሰው ይህንኑ ሥራ እንዲሠራ ይፈቅዳል፣ ለምርት ግብይት ዓላማ የምርት የምስክር ወረቀት ይሰጣል።

፫/ የኢትዮጵያ ደረጃዎችን አጽድቆ ለማውጣት ብቸኛ ሥልጣን የተሰጠው የኢትዮጵያ ደረጃዎች መዳቢ ባለሥልጣን ሥልጣን እንደተጠበቀ ሆኖ የምርት ገበያው በዚህ አንቀጽ የተሰጡትን ተግባራት ያከናውናል።

፬/ የምርት ደረጃን ለማረጋገጥ በምርት ገበያው ተቀባይነት ያገኘ ማንኛውም ሦስተኛ ወገን ወይም ተወካይ በምርት ገበያው ውስጥና ከምርት ገበያው ውጭ በምርት ግብይት ሥራ መሳተፍ አይችልም።

## ፳፬. ስለ ዕቃ ማከማቻና ደረሰኝ

፩/ የዕቃ ማከማቻ መጋዘን ደረሰኞች ሥርዐት አዋጅ ቁጥር ፫፻፸፪/፲፱፻፺፭ አንቀጽ ፳፮ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የምርት ገበያው የግብርና ምርቶች የክብደት አለካክንና የምርቶች ዝርዝር አስተዳደርን ሥራ መሥራት፣ የዕቃዎች መጋዘንን ማካሄድና ለግብይቱ ዓላማዎች የምርት ገበያውን የዕቃዎች ማከማቻ ደረሰኞች መስጠት ይችላል።

፪/ በዕቃ ማከማቻ መጋዘን ደረሰኞች ሥርዐት አዋጅ ቁጥር ፫፻፸፪/፲፱፻፺፭ ለሚኒስቴሩ የተሰጠው የዕቃዎች ማከማቻ መጋዘኖችን የመቆጣጠር ሥልጣን እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የምርት ገበያው የግብርና ምርቶች የክብደት አለካክንና የምርቶች ዝርዝር አስተዳደርን ሥራ ለሚሠራ ሦስተኛ ሰው የምስክር ወረቀት መስጠት ወይም ለግብይቱ ዓላማዎች የምርት ገበያውን የዕቃዎች ማከማቻ ደረሰኞች መስጠት ይችላል።

## 22. Exchange Contracts

1/ The Exchange shall operate with spot and/or future contracts in agricultural commodities.

2/ The Exchange shall develop the grade basis, date and place of delivery of the commodities and other contractual terms for each contract.

## 23. Grading and Certification

1/ The Exchange shall develop and maintain Exchange approved grades and standards for the purposes of trading on the Exchange.

2/ The exchange shall carry out grading and certification or approve a third party to do the same and to issue an Exchange produce certificate for the purposes of Exchange trading.

3/ The exchange shall carry out its duties under this Article without prejudice to the Quality Standards Authority of Ethiopia as the sole government organ mandated to approve and declare Ethiopian standards.

4/ Any third-party exchange-approved grading and certification agents shall not engage in commodity trading within or outside the Exchange.

## 24. Warehousing and receipts

1/ Without prejudice to Article 26 of the Warehouse Receipts System Proclamation No. 372/2003, the Exchange may operate warehouses to carry out weighing and inventory management of agricultural commodities and issues Exchange warehouse receipts for the purposes of Exchange trading.

2/ Without prejudice to the powers of the Ministry to regulate warehouses under the Warehouse Receipts System proclamation No. 372/2003, the Exchange may certify a third-party warehouse operator to carry out weighing and inventory management of agricultural commodities and to issue Exchange warehouse receipts for the purposes of Exchange trading.

፫/ የምርት ገበያው በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የተደገፈ የምርት ገበያ የዕቃ ማከማቻ ደረሰኞች ማስቀመጫ ይኖረዋል ወይም ሌላ ሦስተኛ ሰው ይህንኑ ሥራ እንዲሠራ ይፈቅዳል።

፬/ በምርት ገበያው ተቀባይነት ያገኘ የዕቃዎች መጋዘን የሚያካሂድ ሦስተኛ ሰው በምርት ገበያውም ሆነ ከምርት ገበያው ውጭ በምርት ግብይት መሳተፍ አይችልም።

## ፳፭. ክፍያና ግዴታ መፈጸሚያ

፩/ የምርት ገበያው በባለሥልጣኑ መመሪያዎች መሠረት ግብይቶችን የሥራ ግንኙነት ካለው ወይም ዕውቅና ካገኘ የክፍያ መፈጸሚያ ተቋም ወይም በሦስተኛ ወገን አማካይነት ክፍያንና ርክክብን ይፈጽማል።

፪/ አባላት በምርት ገበያው የውስጥ ደንቦች መሠረት ከምርት ገበያው ጋር የሥራ ግንኙነትና ዕውቅና ካለው የምርት ገበያው የክፊያ መፈጸሚያ ተቋማት የባንክ ሂሣብ ይከፍታሉ።

፫/ በምርት ገበያው የውስጥ ደንቦች መሠረት ክፍያንና ግዴታን ለማስፈጸም ዓላማ፣ አባላት የሥራ ግንኙነትና ዕውቅና ላለው የምርት ገበያው የክፍያ መፈጸሚያ ተቋማት የገቢና የወጪ ትዕዛዞችን እንዲሰጥ የውክልና ሥልጣን የጽሁፍ ማስታወቂያ ለምርት ገበያው ይሰጣሉ።

፬/ የምርት ገበያው የእያንዳንዱን አባል የግብይት አቋም በየግብይት ቀኑ ያስታርቃል።

፭/ የምርት ገበያው በየግብይት ቀኑ ለእያንዳንዱ አባል የመገበያያ አቋምና ሁኔታ መግለጫ በጽሑፍና በኤሌክትሮኒክ ያወጣል።

፮/ የምርት ገበያው የአባላትን የመገበያያ አቋምና ሁኔታ መግለጫዎችን መሠረት በማድረግ ግዴታቸውን እንዲወጡ የሥራ ግንኙነት ላላቸው የክፍያ መፈጸሚያ ተቋማት መመሪያ ይሰጣል።

፯ የምርት ገበያውና አባላቱ የሥራ ግንኙነት ላላቸው የክፍያ መፈጸሚያ ተቋማት ገንዘብ ከአንድ አባል ወደ ሌላ አባል ወይም ከምርት ገበያው የባንክ ሂሳብ ወደ ሌላ የባንክ ሂሣብ የኤሌክትሮኒክስ ትዕዛዝ ማስ ተላለፊያን በመጠቀም ቋሚ መመሪያዎች እንዲያስተላልፉ ይፈቅድላቸዋል።

3/ The Exchange shall maintain an automated central depository of Exchange warehouse receipts or approve a third party to do the same.

4/ Any third-party Exchange- approved warehouse operator shall not engage in commodity trading within or outside the Exchange

## 25. Clearing and Settlement

1/ The Exchange shall clear and settle all transactions on the Exchange either clearing internally with affiliated, recognized Clearing Institutions or through third-party Clearing Institutions, in accordance with the directives of the Authority.

2/ Members shall maintain accounts with any of the affiliated recognized Exchange Clearing Institutions, in accordance with the Exchange by-laws.

3/ Members shall grant written notice of Power of Attorney to the Exchange authorizing the Exchange to issue debit and credit instructions to affiliated recognized Exchange Clearing Institutions, for the purposes of clearing and settlement, in accordance with Exchange by-laws.

4/ The Exchange shall reconcile daily each Member's trading position on trading days.

5/ The Exchange shall generate a written and electronic daily net obligation statement for each Member on trading days.

6/ The Exchange shall, on the basis of the net obligation statement, instruct the affiliated recognized Clearing Institutions to settle the obligations of the Members.

7/ The Exchange and Members shall be allowed to give standing written instructions to affiliated recognized Clearing Institutions to authorize such institutions to transfer funds to and from Member and Exchange Accounts established in these same institutions for the purposes of Exchange transactions, on the basis of an electronic instruction.

፰/ ፊርማዎች ሕጋዊ ውጤት እንዲኖራቸው በእጅ መፈረም እንዳለባቸው የሚያስገድድ ሕግ፣ ደንብ፣ መመሪያ ወይም የአሠራር ልምድ ቢኖርም፣ ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፯/ አፈጻጸም በኤሌክትሮኒክስ ፊርማ ገንዘብ እንዲተላለፍ የተሰጠ ትዕዛዝ ተቀባይነት ይኖረዋል።

፱/ ማናቸውም የክፍያ መፈጸሚያ ተቋም በምርት ገበያውም ሆነ ከምርት ገበያው ውጭ በግብይት ሥራ መሰማራት አይችልም።

## ፳፮. የገበያ ክትትል

የምርት ገበያው በባለሥልጣኑ መመሪያ መሠረት የሚከተሉትን የገበያ መከታተያ ዘዴዎች ይጠቀማል፣

፩/ የአባላትን ዕዳ ለመከታተል የሚያስችል የገበያ ዕዳ መቆጣጠሪያ ሥርዓት፣

፪/ በምርት ገበያው ከተወሰኑት ጣሪያ በላይ ክፍት ቦታዎች እንዳይኖሩ ለማድረግ የሚያግዝ የክፍት ቦታዎች ጣሪያ ሥርዓት፣

፫/ በውል መሠረት ለሚደረግ የዋጋ ለውጥ ጣሪያ የሚወሰን የዋጋ ሥርጭት ጣሪያ፣

፬/ ባለሥልጣኑ የሚጠይቃቸው ሌሎች ተመሳሳይ ዘዴዎች።

## ፳፯. የአደጋ ቁጥጥር አስተዳደር

የምርት ገበያው በባለሥልጣኑ መመሪያ መሠረት የሚከተሉትን የአደጋ መቆጣጠሪያ የአስተዳደር ሥርዓቶችን ይጠቀማል፣

፩/ የእያንዳንዱን አባል አቋምና ሁኔታ የሚያሳይ የአባላት የዋስትና ተቀማጭ ገንዘብ፣

፪/ የምርት ገበያውን ዕዳዎች ለመሸፈን የሚያስችሉ የክፍያ መፈጸሚያ ዋስትና ፈንድ፣

፫/ ለእያንዳንዱ ግዢ በመያዣነት የሚያገለግል ተቀማጭ የመያዣ ገንዘብ፣

፬/ ከተቀማጩ ገንዘብ አንፃር የአባሉን አቋምና ሁኔታ የሚያሳይ የንግዱን የተጋላጭነት መጠን፣

8/ Notwithstanding provisions of any law, regulation, directive or customary practice that requires a signature be handwritten in order to have legal effect or enforceability, signature requirement under Sub-Article (7) of this Article is met if an electronic signature is used to authorize fund transfers.

9/ Any Clearing Institution shall not engage in trading activity within or outside the exchange.

## 26. Market Surveillance

The Exchange shall, in accordance with the Authority's Directives, establish and maintain the following market surveillance tools:

1/ market loss monitoring, which is a system to track losses of Members:

2/ maximum open positions; which is a system to avoid build up of open positions above Exchange-specified limits:

3/ price spread limit, which limits allowable price variation on a contract; or

4/ other similar tools as the Authority may require.

## 27. Risk Management

The Exchange shall, in accordance with the authority's Directives, establish and maintain the following risk management systems:

1/ member security deposits, a deposit which determines each Member's exposure:

2/ settlement guarantee fund, which guarantees net settlement liability of the Exchange;

3/ margin requirements, a deposit that serves as collateral for each transaction;

4/ trading exposure limits, which monitors Member exposure relative to the security deposit;

፭/ በገበያ ቀናት በገበያው ውስጥ የሚፈጸሙ የቀን ተቀን የተጣሩ ግዴታዎች፣

፮/ በምርት አቅርቦት ረገድ ዲሲፕሊንን ለማስከበር የሚያግዝ ግዴታን ባለመወጣት የሚጣል ቅጣት፣

፯/ ባለሥልጣኑ እንዲሟሉ የሚጠይቃቸው ሌሎች ሥርዓቶች።

## ፳፰. ስለክርክር አፈታት

፩/ የምርት ገበያው ከምርት ግብይት ጋር የተያያዙ ክርክሮች በሽምግልና ዳኝነት የሚፈቱበትን መመሪያና ሥርዓት በባለሥልጣኑ አጽድቆ ያወጣል።

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፩/ መሠረት በምርት ገበያው የሚወጣው የሽምግልና ዳኝነት መመሪያና ሥርዓት በተለይ የሚከተሉትን ማካተት አለበት፣

ሀ/ የሽምግልና ዳኞችን ተፈላጊ ችሎታና የአመራረጥ ሥርዓት፣
ለ/ የሽምግልና ዳኝነቱ የሚመራበትን ሥርዓት፣
ሐ/ ከሽምግልና ዳኝነቱ ጋር የተያያዙ ወጭዎች ስለሚሸፈኑበት ሁኔታ።

፫/ የምርት ገበያው በዚህ አንቀጽ መሠረት ለሚካሄደው የሽምግልና ዳኝነት የጽሕፈት ቤት አገልግሎት ይሰጣል።

## ፳፱. ስለዋስትና

የምርት ገበያው የግል፣ የፋይናንስ፣ የግብይትና ሌሎች ከምርት ገበያው ጋር የተያያዙ መረጃዎች የሚጠበቁበትን ሥርዓት ያቋቁማል፣ ይጠብቃል፡

## ፴. የምርት ገበያውን አሠራሮች ስለመለወጥ

ከሚከተሉት ጉዳዮች ጋር የተያያዙ የምርት ገበያውን አሠራሮች ለመለወጥ በቅድሚያ የባለሥልጣኑን ፈቃድ ማግኘት ያስፈልጋል፣

፩/ የምርት ገበያው መመሪያዎችና የውስጥ ደንቦች፤

፪/ አባልነት፤

፫/ የአገልግሎት ክፍያዎች፤

5/ daily settlement of net obligations on market positions on trading days;

6/ delivery default penalties, which enforce discipline in delivery of goods; or

7/ other similar systems as the Authority may require.

## 28. Dispute Resolution

1/ The Exchange shall, subject to the approval of the Authority, establish rules and procedures for the resolution of disputes arising from exchange transactions through arbitration.

2/ The rules of arbitration to be established by the Exchange under Sub-Article(1) of this Article shall, in particular, prescribe:

a) the qualifications and manner of appointment of arbitrators;
b) the procedures of the arbitration proceedings: and
c) the payment of arbitration related costs.

3/ The Exchange shall provide secretarial services for any arbitration proceeding to be conducted pursuant to the provisions of this Article.

## 29. Security

The Exchange shall provide and maintain a system for protection of personal, financial, trade and other data relating to the affairs of the Exchange.

## 30. Changes to the Operations of the Exchange

The prior approval the Authority shall be required to change the operations of the Exchange with respect to:

1/ the by-laws and rules of the Exchange;

2/ membership;

3/ fees;

፬/ የግብይት ሥርዓት፤
፭/ ለምርት ገበያው የተዘጋጁ ውሎች፤
፮/ የገበያ መረጃዎች ሥርጭት፤
፯/ የክፍያና የርክክብ አፈጻጸም፤
፰/ የክርክር አፈታት፣ እና
፱/ ዋስትና።

## ክፍል አራት
## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### ፴፩. ደንብና መመሪያ የማውጣት ሥልጣን

፩/ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ይህን አዋጅ ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ ደንቦችን ያወጣል፤

፪/ ባለሥልጣኑ ይህን አዋጅ ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ መመሪያዎችን ያወጣል።

### ፴፪. ተፈጻሚነት የማይኖራቸው ሕጎች

የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎች የሚቃረን ማናቸውም ሕግ፣ ደንብ፣ መመሪያ ወይም የአሠራር ልምድ በዚህ አዋጅ በተመለከቱት ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖራቸውም።

### ፴፫. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

**አዲስ አበባ ነሐሴ ፳፱ ቀን ፲፱፻፺፱ ዓ.ም**

**ግርማ ወልደጊዮርጊስ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

4/ trading system;
5/ contracts traded on the Exchange;
6/ market information dissemination;
7/ clearing and settlement;
8/ dispute resolution; and
9/ security.

## PART FOUR
## MESELLANEOUS PROVISIONS

### 31. Power to issue Regulations and Directives

1/ The Council of Ministers shall issue Regulations necessary for the implementation of this Proclamation.

2/ The Authority shall issue directives necessary for the implementation of this Proclamation.

### 32. Inapplicable Laws

No law, regulation, directive or practice shall, in so far as it is inconsistent with this Proclamation, be applicable with respect to matters covered under this Proclamation.

### 33. Effective Date

This Proclamation shall come into force up on Publication in the Federal Negarit Gazeta.

**Done at Addis Ababa, this 4th day of September, 2007**

**GIRMA WOLDEGIORGIS**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**